# የጥምቀት በዓል

## *(የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት በዓል በኢትዮጵያውን እይታ)*

*በጥር ፩ ፳፻፮ (ጥር 1 2006 ዓ.ም.) የተጻፈ በድጋሜ የቀረበ*
*(January 9, 2014)*

“ይደልወነ ንፈጽም ኵሎ ጽድቀ”
“ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናል” (ማቴ ፫፡፲፬_፲፭)

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ
nigatuasteraye@gmail.com
ጥር ፩ ፳፻፮ ዓ.ም.

## መግቢያ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ውሀ በዮሐንስ እጅ እንደተጠመቀ እንኳን ክርስቲያን፤ ከክርስትና እምነት ውጭ የሆነ ሁሉ ያውቀዋል። ክርስቲያን ነኝ የሚል ሁሉ ይሰብከዋል። የጥንት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አበው በሰሩልን ስርአት እኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህናት፤ ከዓለም ልዩ በሆነ መንገድ በስብሸባ በዝማሬ፤ አዛውንቱ በይባቤ፤ ሴቱ በዕልልታ፤ ጎልማሶች በሆታ ሁላችንም ጥምቀት የተሸከመችውን ጥልቅና ምጡቅ ምሥጢር በከፍተኛ ስሜት እናንጸባርቃታለን። ከጥምቀት ምሥጢር ጋራ የተወሀደውን የኢትዮጵያዊነትን ስሜት ለባእድ ግልጽ አድርጎ ለማቅረብና ትውልዱን ለማስተምር ከዚህ ዘመን የከፋ ዘመን ኢትዮጵያን እና ቤተ ክርስቲያናችንን የሚገጥማቸው አይመስለኝም።

የተሸከመውን የበዓሉን መልእክት ይዘት እና ጥልቀት ለወዳጅ ለጠላት ግልጽ አርጎ ለማቅረብ ለትውልዱም ለመመስከር በቤተ መቅደሱና በአውደ ምህረቱ የምንቆም ካህናት ምን ያህል እንደገባንና ብቃታችንን እንመርምር። እራሳችንንም እንጠይቅ።

የጥምቀቱን ምሥጢር ከሊቃውንቱ እንደተማርኩት ከኢትዮጵያዊነት ብሄራዊ ስሜት ጋራ ተዋህዶ የኢትዮጵን ክብር ከሚያንጸባርቁት ነገሮች አንዱ መሆኑን ሲነገር ሰምቼ ቢሆን ኖሮ፤ ሰአቴን ባላጠፋሁ፤ በድረ ገጾች ያቀረቡትን ወገኖች ለማድከም ባልሞከርኩ ነበር። ክርስቶስ ሲጠመቅ የወጃት ጽድቅ፤ ዛሬ በኢትዮጵያ ላይ ሲደረግ ከማየውና ከምሰማው ጋራ በመጋጨቷ በኢትዮጵያውያን እይታ በሚል ርእስ ይህችን ጦማር እንዳቀርበት ተገደድኩ።

### *ኢትዮጵያውያን የሚባሉት እነማናቸው?*

የጥምቀትን በዓል በኢትዮጵያውያን እይታ ብየ ስላቀረብኩት፤ ኢትዮጵያውያን የሚባሉት እነማናቸው? የትኛውንስ ጎሳ እይታ ነው የማቀርበው? ስለዚህ መጀመሪያ ይህ ጥያቄ መመለስ ያለበት ይመስለኛል።

ክፉ ነገር በማድረግ ላይ ላለ ሰውም ሆነ ድርጅት ለንስሀ ካልሆነ በቀር ባለበት እንዲቆይ እድሜ ይስጠው አይባልም። ስለዚህ የወያኔን እድሜ ያሳጥረውና ኢትዮጵያ "የምትባል አገር የለችም ብትኖርም ካጼ ምንይልክ ወዲህ ነው" በሚለው ሰይጣናዊ （ስብከት ለደግ ነው። ይህ ግን ስብቀት ይባላል） ስብቀቱ፤ ኢትዮጵያዊነታቸውን የካዱ የዜግነት ህብረታቸውን የናዱ ስላሉ፤ የኢትዮጵያዊነትን ማንነትና ምንነት ሳንረዳ ወደ ጥምቀቱ እይታ መሻገሩ ጽሑፉን መሰረት ያሳጣዋል።

ኢትዮጵያዊ የሚባለው የየትኛው ጎሳ አካል ነው? የኢትዮጵያውያን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ነቢዩ ኤርምያስ ኢትዮጵያን ከነብር ጋራ እያነጻጸረ የተናገረውን ባንድምታ ትርጉማቸው፤ የኢትዮጵያዊነትን ዝንጉርጉርነት የሚገልጹት፤የቀለሞች፤ የቋንቋዎች፤ የእምነቶች እና የጎሳዎች ዝጉርጉርነት ባንድ ነብር አካል ላይ እንደሚታይ ውበት አርገው ነው። ከዚህ በታች በሰፈረው እንዲህ እያሉ ይገልጹታል።

"ከክርስትና በፊት አክሱም በሩቅ በምትፈልቅበት ዘመን፤ ከሩቅ እና ከመካከለኛው ምስራቅ እንዲሁም ከሚያዋስኗት አገሮች፤ ብዙ የተለያዩ የሰው ዘሮች ገብተውባታል። በነበራት የንግድ የፖለቲካ እና የባህል እንቅስቃሴ ህዝቡ እርስ በርሱ እየተካካበና እየተሳሰረ እስከ ዘመነ ዮዲት ደረሰ።

በስምንተኛው ክፍለ ዘመን ዮዲት አኩስ ን እንዳልነበረች ስታደርጋት ይህ ሲካካብና ሲተሳሰር የኖረ ህዝብ፤ ወደ ኋላ እየተመለሰ ዘር በመቁጠ ቀይ ባህርን ተሻግሮ ወደ መጣበት አልተመለሰም። ወደ መሀል አገር ገብቶ ተበትኗል። ባረፈበትና በየደረሰበት እየሰፈረ ካካባቢው ጋራ እራሱን እያስማማ እስከ ዘመነ ግራኝ ወረራ ደረሰ።

ግራኝ መሀመድ ከምሥራቅ ተነስቶ የምስራቁን ህዝብ ሰራዊት አድርጎ አገሪቱን በወረረ ጊዜ ከሱ ጋራ የዘመተው እስከ ሰሜኑ ጫፍ ድረስ ዘልቆ በመሄድ በየደረሰበት ንብረት እያፈራ መኖር ጀመረ። ወደ ተነሳበት መንደሩ አልተመለሰም።

ይህም ብቻ አይደለም በዘመነ መሳፍንት በነበረው ትንቅንቅ አንዱ ሌላውን አሸንፎ ለማስገበር ሲል በፈጸመው የእርስ በርስ ወረራ፤ በኢትዮጵያ ምድር የአራዊት ባህርያት ጎልተው በታዩባቸው ወቅቶች በማነኛውም ጎሳ (ባይሆን እንኳ ጡት መቁረጥ እንጅ) ሴት መግደል ነውር ስለነበረ፤ አረሞው ባማራው ላይ ሲዘምት ወንዱን እየገደለ ሴቱን እየማረከ በመውሰድ የማረካቸውን ፳ ስድስቱን ሴቶች ለቆሮዎችና ለጄሌዎቻቸው በማሰራጨት ያድሉ ነበር።"

አማራውም በለስ ሲቀናው የሴቶችን ጡት አይቁረጥ፤ የወንድ ብልት አይስለብ እንጅ፤ ግድያንና ማሰቃየትን እየተጠቀመ ሴት የመግደልን ነውርነት አክብሮ፤ የማረካቸውን ፳ ስድስቱን ሴቶች ለጎበዝ አለቃው ለጭቃ ሹሙ እቁባት እያደረገ ይረጭ ነበር። ከዚያም በኋል ከቤተ መንግስት ጀምሮ እስከ ወያኔ ዘመን ድረስ የነበረው የኢትዮጵያ ህዝብ በራሱ ፈቃድ እየተዋደደ እና እየተፋቀረ ከተወሳሰበው （ከተጋባው） የመነጨ ህዝብ ነው።

*በነገራችን ላይ <u>ወሲብ</u> በስምምነት በህግ በጋብቻ በፍቅር ለሚፈጸም ሩካቤ ሥጋ እንጅ የሴቷን ፈቃድ ሰብሮ ና ገስሶ ለሚፈጸም ገላጭ ሆና የምትሰጥ አይደለችም። በዘመናችን <u>ወሲብ</u> የምትባለው ቃል በእንስሳ ባህርይ ለሚፈጸም ሩካቤ ተሰጥታ ወንዶች ሴቶችን አስገድደው ለሚፈጽሙት መግለጫ ተደርጋ ስትነገር ትሰማለች። ካባቶች የሰማሁት ግን ያለ ሴቷ ፈቃድ በወንድ ግዳጅ የሚፈጸመው ሩካቤ ድንገት ዘሎ ጉብ ማለትን የምታሳይ "ስሪያ" የምትባለው ቃል ስለሆነች፤ ሰረረ የምትለውን ቃል በመጠቀም ስሪያ ሲሉ እንጅ ወሲብ የምትለውን ቃል ሲናገሩ አልሰማሁም። በወሲብ ፋንታ ስሪያ ብትባል ተስማሚ ትመስለኛለች።*

በኢትዮጵያ ምድር ተወልዶ ያንዲት ነብር አካል ዝዝጉርጉርነት ውጤት አይደለሁም፤ ይህ ዝጉርጉርነት አይነካኝም የሚል ሰው ካለ፤ እኔ አይደለሁም ነቢዩ ኤርምያስ ከግንድ፤ ወይም ከድንጋይ ስር፤ ወይም ከሰማይ ዱብ ያልክ ወፍ ዘራሽ ነህ ይለዋል። የጥምቀትን በዓል የምናየው በወፍ ዘራሾች እይታ ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብ በመነጨበት ዝጉርጉርነት እይታ ነው። ባንዲት ነበር አካል ላይ እንደሚታይ የውበት ዝጉርጉነት እይታ ኢትዮጵያ ያለፈችባቸውን ሶሶት ህግጋት ፩ኛ ሕገ አራዊትን ፪ኛ ሕገ ኦሪትን ፫ኛ ሕገ ክርስቶስን እንመለከታለን።

# <u>ኢትዮጵያ ያለፈችባቸው ሕግጋቶች</u>

<u>፩ኛ:-ሕገ አራዊት</u>
<u>፪ኛ:-ሕገ ኦሪት</u>
<u>፫ኛ:-ሕገ ክርስቶስ ብለው በሶስት ከፍለውታል።</u>

## በሕገ አራዊት ዘመን በሕሊናቸው ዳኝነት ይመሩ የነበሩ ጥቂት ሰዎች ስለተከሰቱ ያ ዘመን ዘመነ__አበው ወይም ሕገ__ልቡና በመባል ይታወቃል። በዓለም ላይ የሚበዛው

የሕገ አራዊት መመሪያ ነፍስ መግደል፤ ውሸት እያፈለቁ መናገር። በእውነት አለመቆም፤ እውነትን መሸሸ፤ መደበቅ፤ መሰወር እና ራስን መውደድ ናቸው። እነዚህም ጠባያተ__ፍጥረት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰይጣን እንደሆኑ ከዚህ በታች እንዲህ እያለ ገለጻቸው።

፩ኛ፡- "ውእቱሰ ቀታሌ ነፍስ ሰብእ" "እሱ ነፍሰ ገዳይ ነው"

፪ኛ፡- "ውእቱ እምትካቱ ኢይቀውም በጽድቅ እስመ አልቦ ጽድቅ በሀቤሁ"

"ሀሰት የተፈጥሮ ባህርዩ ስለሆነች፤ እውነት በሱ ዘንድ ፈጽማ የለችም።"

፫ኛ፡- "ወሶበሂ ይነብብ ሐሰተ እምዚአሁ ይነብብ እስመ ሀሳዊ ውእቱ ወአቡሃ ለሀሰት"

"የሀሰት ምንጭ ነውና፤ ሀሰት ሲናገር ከተፈጥሮ ባህርዩ እያመነጨ ይናገራል።"

እያለ የሰይጣንን ባህርይ ደጋግሞ ከገለጸ በኋላ፤ የተከታዮችን ባህርያት ደግሞ እንደሚከተለው ገልጿቸዋል።

፩ኛ "አንትሙሰ እም አቡክሙ ሰይጣን አንትሙ ወፍትወቶ ለአቡክሙ ትገብሩ።

"እናንንተ የሰይጣን ልጆች ናችሁ። ያባታችሁን የሰይጣን ፍላጎት ትፈጽማላችሁ።"

፪ኛ "አንትሙሂ ዘርኢክሙ በሀበ አቡክሙ ትገብሩ"((ዮሐ ፰፡፴፰__፵፬)

"ካባታችሁ ያያችሁትንና የሰማችሁትን ታደርጋላችሁ"

፫ኛ "ወዐሳብሰ ይኀይይ እስመ ዐሳብ ውእቱ ወኢየሀዝኖ በእንተ አብግዕ"

"ቅጥረኞች ስለሆናችሁ ስለ (በግ) ለወገን ደንታ የላችሁም"

እያለ የህገ አራዊትን አስፈጻሚዎች ይገልጻቸው።

ህገ አራዊት በመጀመሪያው ሰው በአዳም ቤት ሰብ በአቤል እና በቃኤል ህይወት ተከሰቱ። ቃዔል በህገ አራዊት ተገፍቶ ወንድሙን አቤልን አጠፋ። ራሱንም በህገ አራዊት ለመምራት ወደጫካ ገባ። ከዚያች ቅጽበት ጀምሮ ዓለም የነብር እና የዓንበሳ ከተማ ሆነች። ጉልበት የሌለው ጉልበት ላለው ምግብ ሆነ። የሰው ኑሮ በህገ አራዊት በአንበሳና በሚዳቋ፤ በነብርና በበግ ግልገል፤ በበይና በተበይ ግንኙነት መካከል ላይ ተመሰረተ። ሰው በበይና በተበይ ግንኙነት መኖር ጀመረ። ህገ አራዊት የሆነው የሰይጣን ባህያት የሚጋልባቸው ቃኤልን የመሳሰሉ ሰዎች ዓለምን ተቆጣጠሯት።

በቃኤል ላይ የታየው ይህ ሕገ አራዊት ሳይዳስሰው ያለፈ ትውልድና ዘመን የለም። በምሳሌነታቸው ሕገ አራዊትን በትውልድ ጭንቅላት ላይ የሚቀርጹ ሰዎች በዝተው መሪነቱንና ምሳሌነቱን ሲይዙ ዘመኑን እጅግ የከፋ፤ ትውልዱንም የሀሰታቸው ደቀ መዛብርት ያደርጉታል። ያገኙትን ሁሉ ሰውም እንስሳም መሬት ሳይቀር እየጋጡ መብላት አልበቃቸው ይላል። ከዚያም አልፈው "ለእመ ሀልቀ ሰብእ ሡዑ ሰብአ" ማለትም "የምትሰዋው ላም ካጣህ ሰውን ሰዋ የሚል፤ ሰው__በላ አምላክ ይፈጥራሉ።

ህገ አራዊት ሆዳሞችን ካጋኘች እንደ አህያ ትጭናቸዋለች። እንደፈረስም ትጋልባቸዋለች። ሚዛናው ፍርድን ይዛ ብቅ ባለችው በህገ አራት ዘመን እንኳ የሕገ ኦሪት አስተማሪዎች እና አስከባሪዎች ነን የሚሉትን ሆዳሞች እንደተቆጣጠረቻቸው "ትቀትሉ፤ ትሰቅሉ፤ ትቀስፉ፤ ትሰድዱ እምሀገር ውስተ ሀገር ከመ ይብጻህ ላዕሌክሙ ደመ ኩሎሙ ጻድቃን ዘተከዕዎ ዲበ ምድር እምደመ አቤል ጻድቅ እስከ ደመ ዘካርያስ ወልደ በራክዩ ዘተክዎ በቤተ መቅደስ ትውልደ አራዊተ ምድር በእፎ ትከሉ አምስጦ እምኩነኔ ገሀነም (ማቴ ፳፫፡፩ __፴፭)" እያለ ክርስቶስ መሰከረባቸው።

# ሕገ ልቡና ወይም ንጽሐ ጠባይ (concious)

በሕገ አራዊት የሚመራውን ህዝብ ታዝበው የራሳቸውን ህሊና ጠብቀው በመታገል በንጹህ ሕሊና ህይወታቸውን የፈጸሙ በጣም ጥቂት ሰዎች ነበሩ። ይሁን እንጅ ከዚህ በታች እንደምንመለከታቸው እነሱም ቢሆኑ ከህገ አራዊት ንክኪ አላመለጡም።

ለምሳሌ፡- "ወሰትየ ወሰክረ ወተአርቀ በውስተ ቤቱ" እንዲል፡- ኖኅ ጠጥቶ ሰከረ። ሰክሮም በልጆቹ ፊት ተዋርዶ ራቁቱን ወደቀ። "ወምድርሰ ሀለወት እምትካት ዕራቃ" ህይወት አልባ እንደነበረችው መሬት ራቁቱን ሆነ። መቸም በመጠጥ አዕምሮውን ስቶ እርቃነ ሥጋውን አጋልጦ አባት በልጅ ፊት ከመውደቅ የከፋ ኃጢአት እንደሌለ ግልጽ ነው።

"ወይቤ ኖኅ ርጉመ ይኩን ከነአን ወገብረ ወነባሬ ይኩን ለአኀዊሁ"( ዘፍ ፱፡፳፪_፳፭) ከዚያ በኋላ በልጆቹ መካከል የገዥና የተገዥ መንፈስን አመነጨ። "ይህ በኖህ ላይ ተደራርቦ የተከሰተው ስህተት፤ ህገ አራዊት እንጅ ህገ ልቡና፤ ወይም ንጽህ ጠባይ የሚባል አይደለም" ይላሉ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አበው።

አብርሃምም “አማን እኅትየ ይእቲ እመንገለ አቡየ ወአኮ እምንገለ እምየ። ወኮነተኒ ብእሲትየ” (ዘፍ ፳፡፲፪) እህትነቷ ባባቴ ጎን በመሆኗ አገባኋት በማለቱ፤ በዘመኑ በሴት በኩል የሚዛመዱ ማግባት ክልክል እንደነበር ቢያሳይም፤ባካባቢው የነበረው ህዝብም “አልቦ ፍርሀተ እግዚ ውስተ ዝ መካን፡ ይቀትሉኒ በእንተ ብእሲትየ” ማለትም “በስፍራው የሚኖረው ህዝብ በህገ አራዊት የሚመራ ነው። ሚስቴ ናት ካልኩ ይገሉኛል እያለ የህዝቡን አራዊትነት ጠቁሟል። “፲፩) ይሁን እንጅ  እውነቱን ለመናገር እስኪጠየቅ አብርሃም መዘግየት አልነበረበትም። ይህን መሳይ ባህርይ ሊቃውንት አበው “የስነ ባህርይ እንክስና” ይሉታል።

የታወቀው የክርስትና መምህር የሆነው ቅዱስ ጳውሎስም፤ ሁለቱም ህገ አራዊትና ህገ ልቡና በሰዎች መካከል እንዳሉ  “ወያርእዩዎ ገቢረ ሕግ እንዘ ጽሑፍ ውእቱ ውስተ ልቦሙ ።ወያርሰሐስሖሙ ልቦሙ ወይቀልዮሙ” (ሮሜ ፪፡፲) በማለት በህገ አራዊትና በህገ ልቡና መካከል ያለውን ትንቅንቅ ጠቆመ። እንዲያውም “አንሰ ሎቱ እትቀነይ በሥጋየ በልብየኒ ወበ ህሊናየ ለሕገ እግዚአብሔር ወበነፍስትየኒ ለሕገ ኃጢአት (ሮሜ ፯፡፳፫) እያለ ሁለቱ የጦር ሜዳቸው አደረጉኝ፤ ህገ አራዊት አሸንፎ  ልቤን መንፈሴን ማርከው። እያለ የራሱን ህሊና ሳይደብቅ፤ በራሱ ህሊና ላይ ይካሄድ የነበረውን ተማሮ ተናገረ።

“ተጻብአ ወተቃተለ ምስለ ዝኩ ሕገ እግዚ ዘውስተ ልብየ ወሀየለ ዝኩ ሕገ ኃጢአት ዘውስተ አባልየ ወጼወወኒ መንገሌሁ(፯፡ ፳፫) በማለት የተሰማውን ተናገረ።ስ “ወአንሰ በሥጋ ወደም ሥዩጥ ለኃጢአት (ሮሜ፯፡፲፬) እየለ ተናዘዘ። የጽድቅ ሐዋርያ መባል ያለበት ይህ አይነት ግልጽነት ያለው ሰው ነው። ለምናደርጋት ነገር ሁሉ ህሊናችን ተከፍሎ ይሟገታል። ህሊናችን ይፈርዳል። እየፈረደብን እናደርገዋለን። ነገር ግን የህሊናችን ትክክለኛ ፍርድ ብንከተል በእግአብሄር ፊት ነጻ ነን አለ። “ወንህነሰ “ቅድሜሁ ናመክሮ ልብነ። ወእመሰ ያርስሀስሀነ ልብነ እምአበሳነ ወየዐብዮ… እመሰ ኢቀልየነ ልብነ ገጽ ብነ በሀበ እግዚአብሔር“(፩ኛ ዮሐ ፫፡፲፱__፳፩) ስብከት ማለት ይህ ነው።

ሕገ ልቡና (ንጽሐ ጠባይ) ምንጩ እግዚአብሔር ነው። “ወአንሰ ዘርኢኩ በኀበ አቡየ እነግር” “ወእመሂ ኮንኩ አነ ጽድቀ እኳንን  እስመ ኢኮንኩ ባህቲትየ አላ ወአብ ዘፈነወኒ” (ዮሐ ፰፡፲፯) “ወዘልፈኒ ሀሎ ምስሌየ ወኢይሀድገኒ አብ ባህቲትየ እስመ አነ እገብር ስምረቶ ዘልፈ” እያለ ክርስቶስ  እንደተናገረው፤ ንጽህ ጠባይ የፈለቀችው ከክርስቶስ እግዚአብሄርነት ነው። ክርስቶስ “እኔ ቅዱስ እንደሆንኩ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ” እያለ መመሪያ (Prolongation of reference) ሰጠ ።

ሕገ አራዊትም ህገ ልቡናም በጽሁፍ የማይወረሱ ናቸው።  እንደ  አሪት ሕግ በድንጋይ ወይም በብራና የተጻፉ አይደሉም። በሰው ህሊና የነበሩ ናቸው። ከላይ እንዳልኩት ከሕገ አራዊት ጋራ በመታገል እየወደቁ እየተነሱ ህይወታቸውን የጨረሱ “የውህቱ ለአቤል ዘተቀትለ በአመጻ፤ ሂሩቱ ለሴት፤ ወምግባቲሁ ለሄኖክ” እየተባሉ። በአባ ህርያቆስ መጽሐፈ ቀዳሴ የተደረደሩት ጥቂት  ፳ ሰዎች እና ነብያት ተጠቅሰዋል።

የኔታ ፍስሐን  የመሳሰሉ ምርጥ ሊቃውንት “ኮነኖሙ ዳእሙ ሞት እምአዳም እስከ ሙሴ ለእለሂ አበሱ ወለእለሂ ኢአበሱ እስመ ኩሉ በአምሳለ አዳም ተፈጥረ” (ሮሜ ፭፡፲፬)  ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ የተናገረውንም መሰረት በማድረግ  እንዳስተማሩኝ፤ “አዳም በተረገመበት ወቅት፤ በአዳም ሰውነት ውስጥ ተደብቃ ከእግዚአብሔር መርገም ያመለጠች ነጭ እንቁ መሳይ የደም ጠብታ፤ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየዘለለች መጥታ ከሀና ማህጸን ላይ ስትደርስ ማሪያም ሆነች”  እያሉ እመቤታችንን ከአዳም ሰውነት ለይተው ለመቁረጥ የሚሞክሩትን የአላዋቂዎችን በግብዝነት ይቃወሙታል። በተለይ“እምአዳም እስከ ሙሴ” “የገደለ ይገደል ያቆሰለ ይቁሰል” የምትለው ሕገ ኦሪት ብቅ ከማለቷ በፊት የነበረውን ሕገ አራዊት የምታሳይ ቀስት እንደሆነች እነ የኔታ ፍስሐ ይናገራሉ። ያም ሆነ ይህ፤ ህገ ልቡና በጥቂት ሰዎች ብትኖርም፤ በሕገ አራዊት ተጽእኖና ቁጥጥር ስር ነበረች ይላሉ።

# ፪ኛ ሕገ ኦሪት፡-

“ኢትግበሩ ዓመጽ በውስተ ፍትሕ ወኢታድልው ለገጸ ነዳይ ወኢታድልዑ ለገጸ ዓቢይ በጽድቅ ኮንኖ ለከልእከ” (ዘሌ ፲፱፡፲፭) ፍርድ አታዛቡ። ድሀም ከዋሸ ድሀ ነው ብላችሁ አትፍረዱለት። ፍርድ ሚዛን ናትና፤ንብረት ያለውም ከዋሸ፤ ንብረት ስላለው አታክብሩት። ፍረዱበት። “ቅድመ ዘሲበት ተንሥእ ወአክብር ገጸ አረጋዊ”(ዘሌ ፲፱፡፴፪) ሽማግሌ ታሪክ መስካሪ፤ ድንበር አደራዳሪ ነውና  አክብሩት ስሙት” የሚለውን እና “የገደለ ይሙት። ዓይን ያጠፋ ዓይኑ ይጥፋ። ጥርስ የሰበረ ጥርሱ ይሰበር” የሚለውን ሚዛናዊ (ርቱዕ ፍትህ) የተጻፈበትን ጽላት ቤተ ክርስቲያናችን ይዛ የነብር እና የዓንበሳ ከተማ ወደ ሆነችው ዓለም ብቅ አለች።

ይህም ማለት አንድ ሰው ጉልበት አለኝ ብሎ የሰው ዓይን ከማጥፋቱ በፊት በራሱ ዓይን መጥፋት ላይ መፍረድ አለበት። ቢገድል መሞት እንዳለበት በራሱ መፍረድ አለበት። ይህች በጽላቱ ላይ የተጻፈች አስቀድሞ በራስ የመፍረድ ፍትህ፤ ከህገ አራዊት ማለትም ካንበሳና ከተኩላ ስርአት የተለየች ሚዛናዊት “ርቱዕ ይደሉ” የተባለችው ሕግ ናት።

## ሀ. ፲ቱ ቃላት የተጻፈበት ጽላት

በዘመነ ኦሪት የሚመለከው አምላክ ዛሬም የምናመልከው ነው። አምልኮቱ ለሚከናወነው ስርአት ማእከል "ፍትህ ርትዕ" (ሚዛናዊ ፍርድ) የተጻበት ጽላት ነበረች። ክርስቶስ የሁሉ ፍጻሜ ነውና "ህግን ልፈጽም እንጅ ልሽር አልመጣሁም" እንዳለው፤ ሁሉንም ጠቅልሎ ለመፈጸም ራሱን መስዋዕት አድርጎ በማቅረቡ "ለእመ ሀልቀ ላህም ሱዑ ሰብአ" የሚለውን ህገ አራዊትንም ፈጽሟል። ሕገ ኦሪት ቢፈጸምም፤ በስሙ መስዋዕት ሲከናወንባት የነበረችው፤ ፈቃዱንና ሃይሉን የገለጸባትን ጽላት ሥጋ የሆነው ቃል ያወጃት ጽድቅ ነግሳበታለች። እኛም ተቀበሉት ብሎ የሰጠነን ሥጋውንና ደሙን በዚህች ጽላት ላይ አንግሰን እንቀበለዋለን። የጽድቅ በሯ በመጥበቡ ከጽድቅ መድረስ ቢያቅተንም፤ ከህገ አራዊት ውጡ! ለማለትም እንደጥምቀት በመሳሰሉ በዓላትና በውጭና በውስጥ በሚነሱት የሰውን ህይወት የሚያደፈርሱ ህገ አራዊት በተከሰቱባቸው ወቅቶች እና ቦታዎች ሁሉ፤ ወደ ፍትህ ርትእ ለመመለስ ጣሩ! ለማለት ቤተ ክርስቲያናችን **፲ቱ ቃላት የተጻፈበትን ጽላት** ይዛ ብቅ ትላለች።

## ለ. ይህ ጽላት አሁን ለምን አስፈለገ?

ጥምቀት የመነጨው በዘመነ ሐዲስ በክርስቶስ ነው። ጽላት የነበረው ማዕከላዊነት በዘመነ ኦሪት ነው። ታዲያ ሁለቱን ማለትም፤ ጥምቀትንና ጽላትን ምን አገናኛቸው? እኛስ ከዓለም በተለየ መንገድ ለምን ሁለቱንም አዋህደን በጥምቀቱ በዓል እናጸባርቃቸዋለን? የሚሉ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ እና መመለስ ያለባቸው ይመስለኛል።

በነገረ መለኮቱ ላይ ያለውን የትርጓሜ ተዋርሶ ከዚህች ጦማር አስከትየ በማቀርባት ጦማር ለማቅረብ ለጊዜው ልለፈውና፤ ህዝባዊ ወደ ሆነው ሀሳብ በመሻገር በጽላት ላይ ያለውን የኢትዮጵያውነትን ስነ አዕምሮ ባጭሩ እንመልከተው።

### ጽላት ከማስመሰልና ከሐሰት ጋራ አንድነት የለውም።

"አሮን ነደቀ ምሥዋዐ አንጻሮ ወአፆደ እንዘ ይብል በዓለ እግዚእ ጌሰም"(ዘጸ ፴፪፡፭) አሮንና ህዝቡ ከህገ አራዊት (እንስሳ) ባለመላቀቃቸው በእንስሳ ምስል እግዚአብሔር ያልፈቀደውን ለህዝብ የማይጠቅም ባዶ በአል ለማድረግ ሰከሩና፤ "ይበልኡ ወይሰትዩ ወተንሥኡ ይዝፍኑ ወይትዋነዩ(፴፪፡፮) በጽላቱ ላይ ከተጻፈው ፍትህ ርትእ ጋራ ተስማሚ ባልሆነ፤ ነገር ግን በሕገ አራዊት እየተገፉ ሥጋቸው የፈቀደውን እያደረጉ ጽላቱን ሊቀበሉ ሞከሩ። ጽላቱ ከሕገ አራዊት ጋራ አንድነት ስላልነበረው ከነሱ ጋራ አልዘለቀም።

"ወሶበ ቀርበ ሙሴ ኀበ ትእይንት ርእዮ ለውእቱ ላህም ወተውኔት ወተምአ ወገደፎን እምውስተ እደዊሁ ክልኤ ጽላተ ወቀጥቀጦን በታህተ ደብር። ሙሴ የአሮ ንና የህዝቡን ህገ አራዊታዊ ባህርይ ባየ ጊዜ ትእግስቱ አለቀ። ተቆጣ ጽላቱን ለቀቀው ሰበረው። "ወነስኦ ለውእቱ ላህም ዘገብሩ ወአውአዮ በእሳት ወሀረጾ ወዘረዎ ውስተ ማይ ወአስተዮሙ ለደቂቀ እስራኤል።((ዘጸ ፴፪፡፳) ጣኦት የተሰራበትን ሰብርባሪ በውሀ በጥብጦ ስራልን ብለው አሮንን ያስገደዱትን ሰዎች አጠጣቸው። ዲዮቅልጥያኖስ የሚወደውን ወርቅ አቅልጦ አባ አጋግዮስ የተባለውን መነኩሴ የጋተው ይህን ምሳሌ በማድረግ እንደሆነ ሊቃውንት ይናገራሉ። ሙሉ ታሪኩን ለማንበብ ከፈለጉ http:// medhanialemeotcks.org ብለው ይፈልጉ ወይም በጉጉል አባ አጋግዮስ ብለው ይፈልጉ።

ሙሴ ሕገ አራዊት ባስከተለው ጥፋት እጅግ አዘነ። "ሙሴ ለአሮን ምንተ ረሰየከ ዘንተ ህዝበ ከመ ታምጽእ ላዕሌሆሙ ኃጢአተ ዓቢየ"፳፩ ማለትም፡- ምነው አሮን ? በዚህ ህዝብ ላይ መከራ ለማምጣት ይህን ለምን አደረክ? ብሎ በአሮን ላይ እጅግ አዘነ። አሮንም "ወይቤሎ አሮን ለሙሴ ኢትትመዓዕ ላእሌየ ለሊከ ተአምር ግእዞሙ ለእሉ ህዝብ።፳፪ ማለትም፡- የዚህን ህዝብ ጠባይ አንተ ታውቅ የለም ? ለምን በኔ ትፈርዳለህ? ብሎ በህዝቡ አመሀይኝቶ ከወቀሳው ሊያመልጥ ሞከረ። በዚህ ምክንያት በበርሀ ወድቆ ቀረ።

"ክርስቶስ የተጠሩ ብዙወች የተመረጡ ጥቂቶች ናቸው" እንዳለው ሰው ከጽድቅ መድረስ ይቅርና ከሚዛናዊቷ ፍትህ መድረስ አልቻለም። በሕገ አራዊት እየተመሩ የሰው አገር ይወሩ የነበሩት የተጠመቁ ናቸው። በክርስትና ስም አገር ይወሩ ለነበሩት እንኳን በጥምቀት ክርስቶስ ካወጃት ጽድቅ ልትደርሱ ከሚዛናዊቷ ፍትህ ገና አለደረሳችሁም ለማለት ጽድቅ የነገሰችበትን ጽላት ከፍ አርጎ ማሳየት አስፈላጊ ሆነ።

በሕገ አራዊት ተሰቃየን፤ ፍትህ ርትዕ ተጠማን እያለ፤ ለሚጮኸው ደቂቀ ዓዳም ከሚዛናዊ ፍርድ (ከሕገ ኦሪት) እጅግ የተሻለች እጅግ የራቀች፤ የረቀቀች እና የጠለቀች ለዚህ ዓለም የምትጠቅም፤ ወደ ሚመጣውም ዓለም የምትሻገር ጽድቅ የተባለችውን መርሆ "ለቀደሙት አትግደል የተባለውን ሰምታችኋል በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል" ((ማቴ ፭፡ ፳፩) በማለት ክርስቶስ እያወጀ መጣ።

# ፫ኛ፡- ሕገ ክርስቶስ (ጽድቅ)፡-

ክርስቶስ "አብርሃም አቡክሙ ተመነየ ከመ ይርአይ ዕለትየ ርእየሂ ወተፈስሀ"( ዮሐ ፰፡፶፮) እንዳለው፤ አብርሃምን የመሳሰሉ በንጽሐ ልቡና በኦሪት ውስጥ የነበሩ ሰዎች ክርስቶስ በጥምቀቱ ያወጃትን ጽድቅ አሻግረው በማየት በተስፋ ተመኟት። የቀሩት ነብያትም "እግዚአብሄር አየ ፍርድም እንደሌለ ተከፋ ሰውም እንደሌለ አየ። ተደነቀ። ስለዚህ የገዛ ክንዱን መድኃኒት አመጣለት ጽድቅም አገዘው። ጽድቅንም እንደ ጥሩር ለበሰ (ኢሳ ፶፱፡፲፮) እያሉ ተነበዩላት።

ክርስቶስ "ብዙዎች ነብያትና ጻድቃን የምታቱትን ሊያዩ ተመኝተው አላዩም፤ የምትሰሙትን ሊሰሙ ተመኝተው አልሰሙም፤እናንተ በማያታችሁና በመስማታችሁ ብጹአን ናችሁ(ማቴ ፲፫፡፲፯) እያለ ይህችን ጽድቅ አይተውና ሰምተው ለምስክርነት ላዛጋጃቸው ክርስቲያኖች ተናገረ።

ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት እነ ቅዱስ ባስልዮስ፤ ይህች ጽድቅ እንዴትና በምን ሁኔታ እንደ አወጃት "እስመ ክርስቶስ ፍጡር ውኢፍጡር ውእቱ። ኅብሩ በ፩ዱ ህላዌ ወአካል ኅቡረ ንብል ኢፍጡር እስመ ውእቱ ቀዳማዊ እምቅድመ ዓለም ወእስከ ለዓለም። ወውእቱ ፈጣሬ ኩሉ ዘሀሎ ወዘሰ ንቤ ፍጡር በእንተ ዘተሳተፈ ሥጋ ድካመነ በሥርአት ዘገብሮ በእንቲአነ . ... ( ፴፫፡ ፪__፲፪) እያሉ አረጋግጠው መሰከሩ።
በጽላቱ ላይ በተጻፉት ፲ቱ ቃላት እንመራለን የሚሉ ሰዎች፤ በዘመነ አራዊት ውስጥ ለነበሩ ሰዎች ከህገ አራዊት እንዲወጡ፤ በህገ ኦሪት የነበሩ ሰዎች ደግሞ ወደ ህገ ክርስቶስ ማለትም ወደ ጽድቅ ይሻገሩ ዘንድ ምሳሌ እንዲሆኗቸው፤ በክርስቶስ ሕግ (ጽድቅ) ያሉ ሰዎች ደግሞ በዘመነ ኦሪት ለነበሩ ሰዎች ምሳሌ ይሆኑ ዘንድ ታዘዙ።

ከህገ አራዊት ተላቀናል፤ ሕገ ኦሪትን ተቀብለናል ያሉ ሰዎች ይሁዲም ይሁኑ ሙስሊም፤ ኦሪት በምታወጀው ፍትህ ርትእ ከምትባለው እርከን ላይ ደርሰዋል፤ በክርስቶስ አምነን ተጠምቀናል የምንል ክርስቲያኖች ግን ከህገ አራዊት ርቀናል፤ ኦሪት ካወጀችው ሚዛናዊ ፍርድም ተላቀን ክርስቶስ በጥምቀቱ ካወጃት ጽድቅ እርከን ላይ ደርሰናል ብለን ነው። እኛ ክርስቲያኖች የምንከተላት ክርስቶስ ያወጃት ይህች ጽድቅ ምንድን ናት ?

## ሀ. ጽድቅ ምንድን ናት?

"ጽድቅ ክርስቶስ መንግስቱን የሚመራበት መርሆ ናት" (ኤር ፳፫፡ ፭)። ጽድቅ በነቢዩ ኢሳይያስ ንግግር እንደተገለጸው (ኢሳ ፶፱፡፲፯__፲፺) በሕገ ኦሪት የታወጀችው ሚዛናውቷ ፍርድ እድገቷን ስትጨርስ የመጣች መርሆ ናት። በነቢዩ ኤርምያስ እንደተገለጠው ጽድቅ የክርስቶስ ሌላ መጠሪያ ስሙ ነናት ( ኤር ፳፫፡፮)። የዲያብሎስን ሽንገላ (ህገ አራዊትን) የምንቃወምባት መሳሪያ ናት (ኤፌ ፮፡ ፲፩። ጽድቅ የህገ አራዊት መንፈስ በጭንቅላታችን እንዳይገባ መከላከያ ጥሩር ናት (ኤፌ ፮፡ ፲፫። ጽድቅ በህገ አራዊት ከመጥፋት ለመዳን ራስ ቁር ናት።ጽድቅ "ኢየሀስስ ተድላ ለርእስየ"(ዮሐ ፰፡፶)። እንዳለው ጌታችን፤ ራስን አስከድታ ለህዝብ ለወገን መቆም የምታስችል መሳሪያ ናት። ቅዱስ ጳውሎስ፤"ከመ ይጼወው ኩሉ ልብ ወሕሊና ወይግነይ ለክርስቶስ ( ፪ ቆር ፲፡፭) እንዳለው፡- ከህገ ኦሪትም ይሁን ከህገ አራዊት ተላቀው ከጽድቅ የደረሱ ክርስቲያኖች፤ በኦሪቱና በህገ አራዊት ላይ ቆመው የቀሩትን ሰዎች ከጽድቅ እርከን ላይ ለማድረስ መማሪያኪያቸው መሳሪያ ናት።

ክርስትናን ከሁሉም እምነቶች ልዩ ከሚያደርጉት አንዱ፤ ክርስቶስ ሲጠመቅ ያወጃት ጽድቅ ናት። ይህም ማለት አንድ ሰው እጽፍ ድርብ ዋጋ የሚያስጠይቅ በደል ቢፈጸምበት፤ተበዳዩ ለተፈጸመበት ተመጣጣኝ ዋጋ መጠየቁን ትቶ፤ የበደለውን ይቅር ብሎ የበደለውን መውደድን ነው። ለዚህም ማስረጃነት ክርስቶስ ራሱ ተሰቅሎ ራሱን የሰቀሉትን ሰዎች የሚያደርጉትንም አያውቁምና ይቅር በላቸው ብሎ እራሱ ከክርስቶስ ከተናገረው የበለጠ ገላጭ ምሳሌ አይገኝም ብለው ሊቃውንቱ ይደመድማሉ።

ሆኖም በቅዱሳት መጻህፍት ቅኔወቻቸውን ያበለጸጉ የቅኔ መምህሮቻችን፤ እኛ ተማሪዎቻቸው እንደነሱ ቅኔያችንን ከተራነት አውጥተን ከፍ ለማድረግ ይረዳ ዘንድ የታሪክ መጻህፍትን ባንድምታ እንድንማራቸው ያስገድዱናል። ቅኔያችንን ከምናበስልባቸው ከብዙዎቹ ቁም ነገሮች አንዱ በመጽሐፈ ነገስት ካልዕ በ፺ኛ ምዕራፍ የተጠቀሱት ምሳርና የእንጨት ቅርፍት ማሳሌ ነው። በውሀው ውስጥ የሰመጠውን ብረት ለማንሳፈፍ ቅርፍቱ ብረቱ ወደሰመጠበት ጥልቀት ውስጥ ሰመጠ። ቅርፍቱ የብረቱን ክብደት ተሸክሞ በመስጠም፤ የራሱን መንሳፈፈ ለብረቱ በመስጠት ብረቱን አንሳፈፈው። በዚህ ላይ የተዘረፈውን ቅኔ ተቀብያለሁ። እራሴም ቀጥሬበታለሁ። ጽድቅ ማለት ይህች ናት።

አትናቴዎስ የተባለው የመጀመሪያውን ጳጳስ ወደ ኢትዮጵያ የላከው ሊቅ "ክርስቶስ ቦአ ውስተ መርገም በእንቲአነ እንዘ ኢይቀርቦ መርገም፡አላ ሰምረ ከመ ይጹር መርገመ ዚአነ ወበእንተ ዝንቱ ተብህለ ከመ ውእቱ ቦአ ውስተ መርገም(፴፡፬) እያለ ገለጸው።

ክርስቶስ የአዳምን ዘር ከሰመጠበት ጉድጓድ ህገ አራዊትና ከዚያም በላይ በጥፋት በመካካስ መጠፋፋትን ከምታውጀው ሚዛናዊ ፍትህ ከተባለችው ሕገ ኦሪት ያላቀቀን ዘንድ እንደኛ ሰው ሆኖ ጽድቅን አወጀለን። "ይእዜሰ እንተ ትሄይስ መልእክተ አድምአ ወለእንተ ተዐቢ ሥርየተ

ኅሩየ፡ ኮነ ወሠርአ ተስፋ እንተ ትኄይስ (ዕብ ፳፡፻)።"ማለትም፡- በክርስቶስ የታወጀችው ህግ ከቀደሙት ህግጋት ከህገ አራዊትና ከህገ ኦሪት የተሻለች ከዚህ ዓለም ዘልቃ የምትሄድ ህግ ናት። ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ከኢትዮጵያዊነት ስነ ልቡና ጋራ ይህችን ጽድቅ እንዴት አገናዘቧት？

## ለ. የጥምቀት አከባበር ስርዓት ግንዛቤ

በዚህች ምድር ላይ ያለ የየትኛውም አገር ሰው በመጮኽ ላይ ያለው፤ ክርስቶስ ያወጃት ጽድቅ ጎደለች ብሎ አይደለም። በህገ አራዊት በጨለማ ተሰቃየን፤ በህገ ኦሪት የታወጀው ሚዛናዊ ፍትህ ተገፈፍን፤ እያለ ነው። የሚያስገርመው ደግሞ ፍትህ ርትዕ አጎደሉብን በህገ አራዊት በደሉን ተብለው በመከሰስ ላይ የነበሩት ተጠምቀናል የሚሉ ክርስቲያኖች ናቸው። በክርስትና ስም ሕገ አራዊትን በመፈጸም ላይ ያሉትን ለማሳፈርና ለመገሰጽ እንኳን ከጽድቅ ልትደርሱ፤ ገና ከአራዊት ህግ አልተላቀቃችሁም የሚለውን መልእክት ለማስተላለፍ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ጽላት ተሸክማ "ወረደ ወልድ" እያለች ማታ ወደ ፈሳሽ ወንዝ ትወርዳለች።

ጽላቱ ማታ የሚወጣበት ምክንያት ኦሪት ፍትህ ርትእን ብታውጅም፤ የዓለም ሰዎች ከጨለማው ስርአት （ከህገ አራዊት） ገና አለመውጣታቸውን ለማሳየት ሲሆን፤ የጸሐይ ኃይል በደመቀችበት እኩለ ቀን ላይ ጽላቱ ወደ መንበሩ የሚመለሰውም በክርስቶስ የታወጀችው ጽድቅ ከሁሉም ሕግጋት እጅግ የከበረችና የደመቀች መሆኗንና እና፤ ዮሐንስ በራዕዩ ያያትን በክርስቶስ ጸሐይነት ሌትና ቀን የምታበራውን መንግሥተ ሰማያትን ለማሳየት ነው።

በጥምቀት የሚፈጸመው ጽድቅ (እንደገና መወለድ) የሚከናወነው በውሀና በመነፈስ እንደሆነ ክርስቶስ ተነግሯል። አባቶች በውሀንና በመንፈስን መካከል ያለውን ምሥጢራዊ ግንኙነት ለራሱ ለክርስቶስ በመተው፤ ግን ጥንተ ፍጥረት "ወመንፈስ እግዚአብሔር ይጼልል መልዕልተ ማይ" የሚለውን "ድህረ ይመጽኡ ይበይኑ" በማለት ያልፉትና፤ አቅማቸው ወደፈቀደላቸው ግንዛቤ በመሻገር፤ "ለምን ወደ ወራጅ ወንዝ ይኬዳል የሚል ቢኖር፤ ውሀ የህወት ምንጭ ነው። በሰርጎ ገብ ጭቃ ይደፈርሳል። እንደዚሁም፤ "ብዙ ተባዙ ዓለምንም ሙሏት" በተባለው መለኮታዊ ትእዛዝና ቃል ኪዳን የሰው ትውልድም እስከ ዓለም ፍጻሜ እየተተካካ መጉረፉን ይጠቁማል። በሰርጎ ገብ ሰይጣናዊ ሀሳብ መንፈሱ ይደፈርሳል" ይላሉ።

"ወመንፈስ እግዚአብሔር ይጼልል መልዕልተ ማይ"በምትለው እና በመሳሰሉት ረቂቃን ነገሮች ላይ፤ አባቶቻችን ተማሪዎቻቸው ሲጠይቋቸው፤ የተማሪዎቻቸውን የማሰብ ችሎታ ላለመግታት መጭው ትውልድ ይተርጉመው፤ ወይም ድረሱበት የሚሏት ፈሊጣቸውን፤ የዘመናችን የስነ ተፈጥሮ ሊቃውንት ውሀን የህወት ፍንጭ ሰጭ አድርገው መጠቀማቸው የምታስገርም ያደርጋታል። በጥምቀት የታወጀችውን ጽድቅ በሽብሸባ በቅኔ በእልልታና በሆታ የሚካሄዱትን ሥርአት ለመግለጽ የዚህች ጦማር አቅም ስለሚገታ በጎልማሶች ብቻ የምትንጸባረቀውን በጣም አስደናቂ የሆነችውን ሆታ ብቻ እንመለከታለን።

## ሐ. ጎልማሶች "አ ሆ !" የሚሏት ከምን ፈለቀች?

ከአኩስም ዘመነ መንግሥት ጀምሮ እየተቀላቀልን ከመጣንበት ጎሳዎች፤ ከጽድቅ ጋራ የሚጋጭ ባህል ይዘን በመምጣት ከተዋህዶው ነገረ መለኮት ጋራ እንዳንጋጭ፤ በተለይ እኛን ካህናቱን እጅግ መጠንቀቅ እንዳለብን ያብነት ትምህርት ሊቃውንት አባቶቻችን ያስጠንቅቃሉ። "አ ሆ !"ንና የመሳሰሉትን ከነገረ መለኮቱ ጋር የማይጋጩትን ለህዝብ እንድናስተምር በአጽንኦ አደራ እያሉ፤ ኢትዮጵያውያን ጎልማሶች በጽላቱ ዙሪያ "አሆ ！" የሚሏትን እንዲህ ይገልጿታል።

"አ ሆ" የምትለው ቃል፤ ቃለ አጋኖ እና ቃለ አህስሮ ትባላላች። ማለትም ተደናቂ የሆነውን ሰውም ሆነ አስደናቂውን ነገር አክብሮና አጋኖ ለመቀበል። አጸያፊና አስቀያሚ ነገር የሰራውን ሰራውንና የተሰራውን ነገር አቃሎ አዋርዶና ተጸይፎ ለመጣል የምታስችል የስሜት ገላጭ ቃል ናት።

በጥምቀት በአል በጽላቱ ዙሪ የሚደረገው ሆታ ቢቻል ጽድቅን፤ ባይቻል ደግሞ ሚዛናዊ ፍርድ የምትሰብከውን ሕገ ኦሪትን መቀበልን ያንጸባርቃል። "ለእመ ሀልቀ ላህም ሱዑ ሰብአ" ማለትም፤የምታርደው እንስሳ ካጣህ ሰው እረድ" የምትለውን ህገ አራዊትን ንቆ አቃሎ አዋርዶ የመጣልን መልእክት ይወነጭፋል። ይህን ያስተማሩ በጥምቀቱ ያወጃትን ጽድቅን እንዲያስተምሩ ክርስቶስ ሑሩ ብሎ ወደ ዓለም የላካቸው ሐዋርያት ናቸው።

፩ኛ፡- ቅዱስ ጳውሎስ "አ ሖ! ትብልዋ ወኀበርክሙ ተአብሱ አግብርቲሁ አንትሙ ትከውኑ ለሞት"(ሮሜ ፮፡፲፮) በህገ አራዊት መርኋቸው እየተመሩ በደል ከሚፈጽሙ ጋራ ብትተባበሩ በነፍስ በሥጋ የታሪክ የሞራል ሙታኖች ናችሁ። ስለዚህ "አ ሖ! ብላችሁ በመነሳት ተቃወሟቸው እንጅ አትተባበሯቸው" እያለ ሰበከ።

፪ኛ ራሱ ቅዱስ ጳውሎስ "ወእመሰ ለጽድቅ አሐ! ትብልዋ ወኀበርክሙ ውስተ ሠናይ አግብርተ እግዚአ አንትሙ (፮፡፲፯) ክርስቶስ ባወጃት ጽድቅ በመተባበር አሐ! ብላችሁ ተባብራችሁ ብትነሱ የጽድቅ ሠራዊት ትሆናላችሁ። እያለ ደገመው።

፫ኛ ቅዱስ ያዕቆብም "አ ሆ በልዎ ለእግዚ ወእንብየ በልዎ ለጋኔን ወይጎይይ እምኔክሙ (ያዕቆ ብ ፬፡፯) ስለዚህ የጽድቅ ተቃራኒ የሆነውን ጋኔንን እምቢ በሉት። እያለ በሙሉ ልብ ተናረገው።

ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት "በሕገ አራዊት የሚጫናችሁን ቀንበር "ወእንብየ በልዎ" እምቢ ብላችሁ ስበሩት፤ ቀንበሩን ሊጭንባችሁ የሚሞክረውንም አሳፍሩት" ብለው የሰሩላቸውን ስነ ልቡና፤ ጽድቅ በታወጀችበት በጥምቀቱ በዓል ላይ ኢትዮጵያውያን ኅልማሶች ያካሄዱት የነበረውን እንቅስቃሴ የተመለከቱ የውጭ ጸሀፊዎች የሚከተለውን ምስክርነት ሰጥተዋል።

## መ. የታሪክ ምስክርነት

የኢትዮጵያውያንን ኅልማሶች ሆ ታ! ትርጉምና መሰረታዊ አመጣጥ ከሐዋርያት ትምህርት እንደተወሰደ ከብቸናው የቅኔና የመጽሐፍ ትርጓሜ ሊቅ ከነበሩት የኔታ ፈረደ፤ ከዚያም የመጻህፍት ምስጢር ምንጭ ከነበሩት ከደብረ ሊባኖሱ የኔታ ፍስሀ ብሰማውም፤ እጭንቅላቴ ላይ የደወለው እንግሊዞች በቅዱስ እንድርያስ ስም ኬንያ በከፈቱት ኮሌጅ በቆየሁበት ወቅት የኛን ታሪክ ካጠኑት ከእንግሊዛዊው Dr. Smith እና ኬንያዊው Bishop David Gitaree በሰማሁበት ቀን ነው።Dr. Smith ምዕራባውያኑን ወራሪወችን፤ Bishop David Gitaree ደግሞ አፍሪቃውያን ተወራሪወችን ከሚወክሉ ሊቃውንት ናቸው። ለኔ ቢጤ ለቆሎ ተማሪ፤ ወራሪንና ተወራሪን ከሚወክሉ ከነዚህ ሰዎች ስለ ኢትትዮጵያ ሲናገሩ ከመስማት የበለጠ መታደል ያለ አይመስለኝም። ሁለቱም ከዚህ የሚከተለውን ተናገሩ።

ኢትዮጵያንን ያአጎራብቱ አገሮችን ቅኝ በመግዛት ላይ የነበሩ ምዕራባውያን ባለስልጣናት፤ድንበር እየተሻገሩ ወደ ኢትዮጵያ በመግባት "ኢትዮጵያውያን የጥምቀትን እና የደመራን በዓላት ሲያከብሩ በጽላቱ ዙሪያ ሴቱ "ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ" እያለ በእልልታ፤ ኅልማሰው በሆታ፤ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ፤ ይመለከቱ ነበር። ቅኝ ገዥዎች ድንበር ተሻግረው ሲመጡ ይገዟቸው ከነበረው ህብረተ ሰብ ከህንድ ከግብጽ፤ከኬንያና ከቀሩት ሁሉ ቅኝ ግዛቶቻቸው እየመለመሉ የወታደር ማእረግ በመስጠት በስራቸው ባዘጋጇቸው ተገዥዎች ታጅበው በበዓሉ ላይ የሚካሄደውን ለመመልከት ወደ ኢትዮጵያ ይሻገሩ ነበር። በበዓሉ ዙሪያ በካህናቱ የሚሸበሸውን፤ ኅልማሶች የሚያስተጋቡትን አ ሆ ታ፤ ሴቱ ወንዱ ያሚያንጸባርቀውን እልልታ ትርጉሙን እየጠየቁ በየራሳቸው ቋንቋ ለየመንግስታቸው በመላክ በሊቃውንቶቻቸው ያስመረምሩት ነበር። ተከታይና አጃቢ በመሆን የመጡትም ከቅኝ ገዥዎቻቸው ለመላቀቅ ለነበራቸው ምኞት ለምሳሌነት ይጠቅማቸው ዘንድ በህቡእ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ከቅኝ ገዥወቻቸው እየተሰወሩ ይነጋገሩበት ነበር።

አጎራባች አገሮችን ይገዙ የነበሩት ምዕራባውያን ቢችሉ በጥመቀት በዓል ላይ የሚንጸባረቀውን የነጻነት ስሜት ለማዳፈን፤ ባይችሉ ግን ወደ ጎረቤት አገሮች እንዳይሻገር ለመቆጣጠር የሚችሉበትን መንገድ ለመፍጠር ይጥሩ ነበር። በተቃራኒው የሞራል ሰዎች የሆኑት ፈርንጆች ደግሞ የሚከተለውን ይመዘግቡ ነበር። ከብዙ ጸሐፊወች ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

፩ኛ. Rev Sterling M. Meaus" የተባሉ ጸሐፊ በ1945 ባቀረቡት መጽሀፍ። Ethiopia & the missing link in Africa history በሚል ርእስ "from time immemorial ethiopia has played an important part and often the leading role in the affairs of the world. The bible as well secular history conforms this fact."(Page 100) ብለዋል።ህም ማለት ከጥንት ጀምሮ ኢትዮጵያ በዓለም ጉዳይ ለሰው መሆን እጅግ የተደነቀ ምሳሌነት መሪ የሚሆን ሚና ተጫውታለች"።

በሳቸው አገላለጽ በተለይ "The bible as well secular history conforms this fact." ያሏትን ሀረግ ብንመለከት፤ በ secular history (በዓለማዊው ታሪካችን) የተከሰተውን እንደ ጥምቀት የመሰሉ በዓሎች የተሸከሙት ሚዛናዊት ፍትህ (እኩልነት) ከኛ አልፎ ለነ ማንዴላ የደረሰላቸውን ነጻነት ለመግለጽ ነው። ከዚያም ቀደም ብሎ በራሳቸው ህዝብ የተሳደዱትን ሙስሊም ዓረቦችን የመሲህ ሰዎች የተባሉት ኢትዮጵያውያን እጃቸውን ዘርግተው የተቀበሉበትን ጽድቅ ለማመልከት ነው።

፪ኛ Drusilla Dunjee Houston የተባሉ ደራሲም "wonderful Ethiopians of the ancient Cushite Empire" በሚል ርእስ ባዘጋጁት መጽሀፍ "from remotest times to the present , the Ethiopians have been the most celebrated and yet the most mysterious of nations."(24) ብለዋል። ማለትም፦ ከጥንት ጀምሮ እስካለንበት ዘመን ኢትዮጵያውያን በታሪካቸው እጅግ የተከበሩ እጅግም የረቂቁ ናቸው" ብለዋል።

፫ኛ Iris Habib el Masir የተባሉ የኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ጸሐፊም አስደናቂ ምስክርነት ሰጥተዋል። ከሊቃውንቱ አንዱ ኢትዮጵያዊ ሊቅ በጥምቀቱ በዓል የሚደረገውን የጎልማሶችን ጭፈራ በምእራፍ ፴፩፥፳_፲ ከሰፈረው ከነቢዩ ኢሳይያስ ትንቢታዊ ምንባባ ጋራ በማነጻጸር ያቀረበውን ቅኔ በመረዳት "The true story of Christianity in Egypt 1982 ብለው በጻፉት መጽሀፋቸው ላይ "the sheep of Ethiopia have been delivered from the hayenas of the west by the doctrines of the Apostles and St. Cyril "(page 262) ብለዋል። ማለትም፡-እንደተራብ ጅብ ዓለምን በመብላት ላይ ከነበሩት ምዕራባውያን ጅቦች ኢትዮጵያውያን የዳኑት በቅዱሳን አክትቪስቶች በነ ቅዱስ ቄርሎስ ትምህርት ነው።" ብለዋል።

ነቢዩ መሀመድም፤ ተከታዮቻቸውን ዓረቦች የራሳቸው ወገኖች ባሳደዷቸው ጊዜ "ክርስቶስ በተጠመቀ ጊዜ ያወጀውን ጽድቅ ለመፈጸም የሚጥሩትን የኢትዮጵያውያንን ዝና በመስማት ወደ ኢትዮጵያ ሂዱ ብለው ሸኝተዋቸዋል።

ነቢዩ መሀመድን ካነሳሁ ዘንድ፤ ባንድ ወቅት ዓረቦች ተናገሩ ተብሎ ተጽፎ ባጋጣም አግኝቼ ያነበብኩትን አለመመስከር ስህተት ስለሆነ አላልፈውምና ያንባቢን ትእግስት በመማጸን አቀርበዋለሁ።

ሴንት ሉስ እያለሁ በጣም የማከብራቸው የኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ Father Baslios የሚባሉ ቄስ ነበሩ። ከእለታት አንድ ቀን ልጎበኛቸው ከመኖሪያ ቤታቸው ሄድኩ። በተቀመጥቁበት ወንበር ሆኜ በፊቴ ያለውን ጠረጴዛ ስመለከት በጠረጴዛው ላይ በአረበኛ እና በእንግሊዘኛ ዓረብ አገር ተዘጋጅቶ የተላከላቸውን መጽሄቶች ሳገላብጥ፤ እሳቸው አዩኝና "የራስህ አገር መንግሥት የሚያደርገውን በውስጡ ታገኛለህ" አሉኝ፤ ውስጡን ሳገላብጥ እነ አቶ መለሰ ያደረጉትን ደባ ተጽፎ አነበብኩ።

ታሪኩ እንደዚህ ነው፤ እነ አቶ መለሰ ከኢትዮጵያ ጋራ በሚዋጉበት ወቅት "በናንተ ሙሉ እርዳታ አሸንፈን ኢትዮጵያን ከተቆጣጠርን ኢትዮጵያን የዓረብ ሊግ አባል የምትሆንበትን ህግ አውጥተን እናውጃለን" እያሉ ለዓረቡ ዓለም ቃል ገብተው ኖሮ፤ እንደተመኙት ሆነላቸው እና፤ እንደገቡ ያውጃሉ ብለው እነ አቶ መለሰን ቢጠብቀ‐ ዘገዩ ባቸው። "ለምን ዘገያችሁ ? ብለው እነ አቶ መለሰን ዓረቦች ጠየቋቸው።

እነ አቶ መለሰ የሰጧቸው መልስ "በአገር አንድነት ህዝቡን አስተሳስራ የኖረችውን ቤተ ክርስቲያን ሳናዳክማት፤ በብሄራዊ ወኔ ያስተሳሰረችውንም ህዝብ በመከፋፈል ኃይሉን ሳናፈርሰው ልናውጅ ብንሞክር ለህልውናችን አዳጋች ስለሆነ ጊዜ ስጡን፤ ይልቁን በኢትዮጵያ ያሉት ሙስሊሞች ባለፈው መንግስት እየተገደድን የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ መቅደስን ህንጻ ሰርተናልና እኛም ገብተን እንጸልይ እንዲሉ ግፏቸው። እኛም ሙብታቸው ነው በማለት እስከ በመፍቀድ ድረስ እንገፋለን። በዚህ ሁኔታ ቤተ ክርስቲያንንም ህዝቡንም ካዳከምን በኋል እናውጃለን እንጅ፤ አሁን ብናውጅ እንዳሰብነው አይሆንም" ብለው መልስ እንደሰጧቸው ይገልጻል። ዓረቦች ይህን ታግሰው ከመቀበል ይልቅ በጣም ቸኮሉና፤ እነ አቶ መለሰን ለመርዳት ታጥቀው የሚገቡበትን መንገድ ተሰብስበው ሲነጋገሩ፤ ያካባቢው ሸማግሎች <u>"ነብያችን ሀበሾች እውነተኛ የመሲህ ሰዎች ናቸው እና እንዳትነኳቸው ብለው አዝዘውናል። ቀን ጥሏቸዋል ብለን ይህን የመሰለ ደባ በአበሾች ላይ መፈጸም ከአላህ ጋራ መጋጨት ነውና አቁሙ"</u> አሏቸው።

እነ አቶ መለሰን ለመርዳት ታጥቀው ለመግባት የፈለጉት ዓረቦች "አሁን በኢትዮጵያ ምድር ያለው አበሻ በነቢዩ ዘመን እንደነበሩት የመሲህ ሰዎች አይደሉም። ወደ ፈጣሪ አልባ እምነት ተለውጠዋል። ግማሹ በመስቀል ጦርነት ጊዜ ወደወረረን ክርስትና የተገለበጡ ናቸው ብለው እነ መለሰ ነግረውናል" ብለው እንደመለሱላቸው እና፤ ሽማግሎችም "ምንም ይሁኑ በሀበሻ ምድር ላይ ካሉ እንዳትነኩ" ብለው አስቆሟቸው" የሚል በመጽሄቱ ላይ ተመዝግቦ አነበብኩ።

ኢትዮጵያውያን ሆይ! መጀመሪያ "ከረድችሁን እና አሸንፈን ኢትዮጵያን ከተቆጣጠርን ኢትዮጵያን የዓረብ ሊግ አባል የምትሆንበትን ህግ አውጥተን እናውጃለን"ማለታቸውን፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ "በአገር አንድነት ህዝቡን አስተሳስራ የኖረችውን ቤተ ክርስቲያን ሳናዳክማት፤ በብሄራዊ ወኔ ያስተሳሰረችውንም ህዝብ በመከፋፈል ኃይሉን ሳናፈርሰው ልናውጅ ብንሞክር ለህልውናችን አዳጋች ስለሆነ ጊዜ ስጡን ማለታቸውን፤እስከዚያ ግን የኛን እቅድ በማራመድ እንዲረዱን በአገራችን ያሉት ሙስሊሞችን በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ መቅደስ እኛም ገብተን እንጸልይ እንዲሉ ግፏቸው" ማለታቸውን ስንመለከት፤ የዓረቡን ዓልም ሳይቀር በማታለል ኢትዮጵያን ለማፍረስ እነ አቶ መለሰ ያለ የሌለ አራዊታዊ ባህርያቸውን በግልጽ እንረዳለን። በበኩሌ ይህ እየዘገነነኝ ሳለ፤ አሁን በቅርቡ ደግሞ እነ አቶ መለሰ የዘረጉትን ህገ አራዊት ዶክተር አረጋዊ በርሄ፡-

> *"የትግራይ ህዝብ ነጻ አውጭ ግንባር በ1979 አመተ ምህረት አስተሳሰብ ለዋጭ የፕሮፓጋንዳ መርሀ ግብር ለሚመለምላቸው ቀሳውስት ዘረጋ። የማሰልጠኑ ዓላማ ቤተ ክርስቲያኗን ከህዝብ ለይቶ በመምታት ስፋቷን ማጥበብና በትግሬአዊነት ላይ ብቻ የተመሰረተ ስሜት በትግራይ ተወላጆች ጭንቅላት መክተት ነው። ቤተ ክርስቲያኗ ለረዥም ዘመናት በህዝቡ አዕምሮ ላይ ስትተቀርጸው የኖረችውን ብሄራዊ የኢትዮጵያነትን ስሜት ከትግራይ ህዝብ አዕምሮ ጠራርጎ በጠባቡ ትግሬአዊነት ስሜት በመተካት የቤተ ክርስቲያኒቱን ይዘት እያጠበቡ ራሷን ቤተ ክርስቲያኒቱን መምታት ነው"*
> ብለው የገለጹትን ጽሁፍ አግኝቸ አነበብኩ። ታዲይ የኔ ቢጤ የቆሎ ተማሪ ጭንቅላት እንደሰረዝ ቅኔ የተደራረበውን የነ ገብረ ኪዳን ደስታን ህገ አራዊት እንዴት እና በምን መንገድ ሊገልጸው ይችላል?

በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ መነኮሳትና ሰባኪዎች መስለው ሰርገው ገብተው የነገብረ ኪዳንን አራዊታዊ ተልኮ የሚያራምዱትን በግልጽ እስካየሁ እና የዶ ክተር አረጋዊ በርሄን ጽሁፍ አግኝቼ በማንበብ እስካረጋገጥኩ ድረስ፤ በኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ካገኘሁት መጽሄት ያነበብኩት ሰመመን ይሁንብኝ እንጅ፤ በጣም አልከከነኝም ነበር። የነ ፋሌቅ ወጥመድ በሚል ርእስ ሰኔ ፳፻፬ ዓ.ም. ያቀረብኩትን ጦማር ይመልከቱ።

# መደምደሚያ

ይህች ጦማር ደርሳችሁ የምታነቡ ወገኖቼ! በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ጸንታችሁ እስካሁን ያላችሁ፤ በኛ በካህናቱ ድካምም ይሁን በተለያዩ ምክንያቶች ከተጠመቃችሁባት እናት ቤተ ክርስቲያናችህ ርቃችሁ ያላችሁ፤ በእስልምና እና በኦሪቱ እምንት ያላችሁ፤ በህገ አራዊት ስብከት (ስብቀት) በመሰበቃችሁ የዚያ የዚህ ጎሳ አካል ነን ብላችሁ ሌላውን የጎረጥ በመየት ላይ ያላችሁ፤ በተለያዩ ርእዮተ ዓለማት ተከፋፍላችሁ በጎረጥ በመተታተት ላይ ያላችሁ።

በዮዲት ዘመን፤ ከዚያም በግራኝ መህመድ ዘመን የተደረገውን የዘር መወራረስ፤ በመቀጠልም በመሳፍንቱ ዘመን በተደረገው አንዱን ሌላውን በመማረክና በፈቃድ በተደረገ መወራረስ ሁላችንም የተቀላቀልን መሆናችንን እና ያንድ ጎሳ ውጤት አለመሆናችንን ለማሳየት ያቀረብኩትን ሙከራ በጥሞና እንደተመለካትችሁት ተስፋ አደ ራገለሁ። እኛ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ወገኖቻችሁ ክርስቶስ በጥምቀቱ ያወጃት ጽድቅ በልባችን ተተክላ በጽርሀ አርያም ያለች መሰላላችን ናት ብለን ብናምንም፤ ይህ እምነታችን እንደለ ሆኖ፤በተለያዩ ዘይቤዎች ማምለካችን ለሰው ዘር የሚጠቅም ጽድቃን የታወጀበት የጥምቀት በዓል የሁላችን የጋራ ቅርሳችንና መኩሪያችን ስለሆነ ለቅርስነቱ በህብረት እንድንጠነቀቅለት በትህትና እጠይቃለሁ።

እኛን ያመነጨን ህዝብ በዚህ አይነት ምስቅልቅል ያለፈና ያለፈባቸውን ሶስቱን ህግጋት ማለትም ህገ አራዊት፤ ህገ ኦሪትና ክርስቶስ ያወጃትን ጽድቅ ተመልከተናል። በጨለማው ዘመን የጥንት አባቶቻችን በሰሩት ስርአት ጽላቱን ተሸክመው ወደ ወንዝ የሚሄዱበትንም ምክንያት ተረድተናል።

ይህ ስርአት ከተሰበሰቡት መጻህፍት በላይ ውድና ክቡር ቅርሳች እንደሆን እና አባቶቻችን ከመጻህፍት እጅግ የበለጠ ጥቅም እንዳለው ገልጸውልናል። ሳያውቁ በስህተት አውቀው ብሸፍጥ በሚነጉዱ ሰዎች "መጻህፍት ይሰረቃሉ። በምስጥ ይበላሉ፤ በዝናብም ይደመሰሳሉ። ይቃጠላሉ፤ አንብቦ የሚረዳቸውም ከራሳቸው ካካቢያቸው እና ዓለም ከደረሰችበት ግንዛቤ ጋራ ማገነዝብ የሚችሉ ጥቂት ብቻ ናቸው። በዓላት ግን የሚከናወኑባቸውን በማየትና ስለ ምክንያቱ ሲወራም በመስማት ያልተማረውም ህጻኑም በቀላሉ ይማርባቸዋል። በሸፍጠኞች አይሰረቁም፤ አይደመሰሱም። አይቃጠሉም። ምስጥ አይበላቸውም ይላሉ።

በ University of Cambridge Social Anthropologist የሆኑት Dr. Paul Connerton የተባሉ ሰው "How societies Remember" （1989）በሚል ርእስ በጻፏት መጽሐፍ፤ በዓላት ከመጽሐፍ ባላነሰ ሁኔታ ማስታወሻ መሆናቸውን የተጠቀሙበት አገላለጽ የጥምቀትን በዓል ከሰሩልን ዓባቶቻችን ስሜት ጋራ መስማማቱ እጅግ ያኮራል ያስደንቃልም።

Dr. Paul Connerton የተባሉት እኒህ የትኩረት ሰው፤ ለብዙ ዘመናት በታላቅ ስሜት በህዝብ ሲከበሩ የቆዩ ጥምቀትን የመሳሰሉት በዓላት፤ ፊደል ባልቆጠረ ዜጋ ሁሉ ይነበባል። ሲከበር በሚያዩ ህጻናት አእምሮ ላይ የጥልቀቱ የስፋቱ ምስጢር እያደጉ ሲሄዱ በ Social memory, collective memory, individual memory, በ personal memory እና በCognitive memory ውስጥ የበለጠ ስር ይሰዳል።" አሉ።

በበዓላት ብልጭ የሚሉ ትዝታዎች ባምስቱ ህዋሳቶች በማየት በመስማት በመዳሰስ በመቅመስና በማሽተት አማካይነት ገብተው የሚጎዘጎዙት በዓዕምሮ ብቻ ሳይወሰኑ በህዋሳቶቻችን ሁሉ ላይ ነው። ለበዓሉ በሚዘጋጁት ምግባችን ልብሳችን ቋንቋችን ላይ ይሰፍናሉ። በዘፈን በደስታና በህዘን አዲስና ትኩስ ሆነው እንደገና ይቀሰሳሉ። በመላ ሰውነት በተጎዘጎዘው ትዝታ በመገፋት ጥምቀትን የመሰሉትን በአላት ለማክበር ከጥቂት ሳምንታት በፊት በስሜት ይንቀሳቀሳል። በቅርቡ የደመራው በዓል በዓለም ዓቀፋዊነት እንደተመዘገበ ሰምተናል። ከደመራው በዓል ይልቅ፤ የጥምቀቱ በዓል ያዘለው ምሥጢር እኛን ይቅርና የሰውን ዘር ሁሉ የሚያካትት ነው። አባቶቻችን የሰሩትን ይህን አኩሪ ቅርስ አንዳንድ ሰዎች ሳያውቁ በስህተት፤ እያወቁ በሸፍጥ አፈር ሊያለብሱት ቢሞክሩም፤ የነሱን ከንቱነት ከማሳየት በቀር። ይህን ቅርስ የማይፈልገው፤ የማይሻውና የማያደንቀው ስለሌለ በዓለም ቅርስነት መመዝገቡ የሚቀር አይደለም።

ምዕራባውያን ክርስትናን የተቀበላችሁ ሁሉ ወገኖች ኢትዮጵያውያን ሆይ! ይህ ሊቃውንት አባቶቻችሁ የሰሩት እናትና አባቶቻችሁ ሲከተሉት የነበረው አሁንም ያለው የጥምቀት በአል የሚኮራበት እንጅ የሚታፈርበት አይደለም። ራሳችሁን ከዚህ አግልላችሁ ልጆቻችሁንም ለዚህ ባይታወር ከማድረግ ይልቅ ራሳችሁን ፈትሹ፤ ለልጆቻችሁም አስተምሩት። ለታሪካቸው ለቅርሳቸው ባይታወር አድርጋችሁ አታሳድጓቸው። የደመራው በዓል ዓለም አቀፍ ከሆነ፤ የጥምቀት በዓል የማይሆንበት ምክንያት የለም። ለልጆቻችሁ ሳታካፍሏች ዓለም ቢቀድማችሁ ልጆቻችሁ

ማሰብ ሲጀምሩ ምንያህል እንደሚታዝቧችሁ አትርሱ። ራሳቸው ምዕራባውያን ከራሳቸው ጥቅም አንጻር በፍርሀትና በማንኳሰስ የጎረጥ ቢያዩትም፤ ሚዛንን የተከተሉ ሊቃውንቶቻቸው ግን በብራቸው መስከረውለታልን ልናፍረበት አይገባም። ይልቁንም እንደ ደመራው በዓል የጥምቀት በአላችንም፤ ዓለም አቀፍ እንዲሆን በምናደርገው ጥረት ተባበሩን።

- <u>በህዝባዊ አገልግሎት ላይ ያላችሁ ወገኖች ሆይ!</u>

ኢትዮጵያን ከወደቀችበት ህገ አራዊት ለማውጣት በየበሩ ቆማችሁ በመታገል ላይ ያላችሁ ሁሉ! ደፈርከን አትበሉኝና፤ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን በዓለም ባለው የሰው ዘር ልብ ውስጥ የጻፉትን ቅዱስ ስርአት በመናቅ በመሸሸ የየራሳችሁን ጽድቅ ለመትከል አትሞክሩ። እነ አቶ መለስ የተከሉትን ህገ አራዊት ከኢትዮጵያ ነቅላ የምትጥለው ይህች በጥምቀቱ በዓል የምናንጸባርቃት ናት። ለኢትዮጵያ የሚዋጋላት ይህን ጽድቅ መርሆ በማድረግ የሚንቀሳቀስ ሠራዊት ነው። ከአንበሳ የተረፈ ቅንጥብጣቢ ለቃቃሚዎች ቀርቶ፤ የሲኦል ደጆች የተባሉት ኃያላንም ይህችን ጽድቅ ሳያሸንፏት ዘመናት ማቋረጧን ልንረሳ አይገባም።

ከውጭ የቀሰማችሁትን ጠቃሚ ትምህርት አባቶቻችን በሰሩልን በጥምቀት በዓል በምትከበረው ጽድቅ ላይ መስርቱት፤ ህዝባችሁንም በዚህ አንቀሳቅሱት። ይህን ብታደርጉ ቅዱስ ጳውሎስ “ዑቁ እንከ ርእሰክሙ በእንተ አንብቦ ወዘልፈ ሀሉ ባቲ። ወእመሰ ዘ ንተ ገበርከ ርእሰከሂ ታድኅን ወዘኒ ይሰምአከ (፩ጢሞ ፬፡፲፮) ብሎ የተናገረው ይፈጸምላችኋል።

- <u>ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ወገኖች ሆይ!</u>

ድፍረት አታርጉብኝና፤ ነቢዩ መሀመድ የእምነት አባቶቻችሁ የነበሩትን ዓረቦች ወደ ኢትዮጵያ ሂዱ አምልጡ ብለው ሲሸኟቸው፤ ከኢትዮጵያውያን ውጭ ክርስቲያን ነኝ የሚል በዓለም ስላልነበረ አይደለም። ንብያችሁ ይህን ያሉት፤ በጥምቀቱ በዓል አማካይነት በሥጋ በወለዷችሁ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችሁ ልብ ላይ ተተክላ ታንጸባርቅ የነበረችውን የጽድቅ ነጸብራቅ በመስማታቸው ነው። ስለዚህ በእምነት ብንለያይም በተመሰቃቀለው ዘራችን አንድ መሆናችን ካለመዘንጋት ጋራ፤ የእምነት አባቶቻችሁ ዓረቦች ተሰደው ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ፤ የሥጋ አባቶቻችሁ ኢትዮጵያውያን ያቀፉባት ክርስቶስ ሲጠመቅ ያወጃት ጽድቅ ስለሆነች፤ የጥምቀትን በዓል እንደ ቅርሳችሁ ልትጠብቋት ይገባችኋል።

እኛ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ወገኖቻችሁ፤ ብንችል መሲህ ካወጃት ጽድቅ ዝንፍ እንዳንል፤ ካልቻል ደግሞ ፆሪት ካወጀችው ሚዛናዊት ፍርድ በታች እንዳንወድቅ በርቱ እንበርታ ልትሉን ከፍተኛ እዳ አለባችሁ። እነ አቶ መለስን ለመርዳት ታጥቀው የሚገቡበትን መንገድ ተሰብስበው ሲነጋገሩ፤ ያካባቢው ሽማግሎች <u>“ነብያችን ሀበሾች እውነተኛ የመሲህ ሰዎች ናቸው እና እንዳትነኳቸው ብለው አዝዘውናል። ቀን ጥሏቸዋል ብለን ይህን የመሰለ ደባ በአበሾች ላይ መፈጸም ከአላህ ጋራ መጋጨት ነውና አቁሙ” ብለው የዓረብ ሽማግሌዎች የተናገሩትን እስላማዊውን ያደራ ቃል ከናንተ ከወገኖቻችን የበለጠ እንደምንጠብቅ አትዘንጉ!።</u>

*<u>በዚህ ዘመን ከኔ ጀምሮ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ውስጥ ያለን ካህናት፡-</u>*

<u>መነኮሳት ሆይ!</u> እናንተም ደፈረን አትበሉኝና፤ መጻህፍቶቻችን የሚያውቋችሁ በገዳማዊ ኑሯችሁ ነው። በከተማ ኑሯችሁ አይደለም። “አርጋኖነ ዲያብሎስ እልያማስኑ ሕሊናተ ርቱዓተ” የተባሉት በህገ አራዊት የሚመሩ ሰዎች በከተማ በገጠር ባሉት ክርስቲያኖች ላይ ስለሚፈጥሩት ቀውስ፤ ከገዳማችሁ ሳትወጡ እንድትጸልዩ ነው። (ሃይ ምዕ ፻፪፡፵_፵፩)

ጸሎታችሁ ከደመና በታች ሳይወድቅ ያለ አንዳች እንቅፋት ቅድመ እግዚአብሄር ሊደርስ የሚችለው “መቅድመ ኩሉ ይርኅቁ ጻ ድቃን ወመነኮሳት እምአንስት ወኢይቅረቡ ኅቤሆን ወኢትናገሩ ምስሌሆን ወይርሀቁ እምኔሆን ከመ ኢያውስኦን ምንተኒ ግሙራ “( ምዕ ፳፡፮) ለሚለው መመሪያችን ተገዥ ስትሆኑ ብቻ ነው።

እኛም ጸልዩልን ልንላችህ የምንችለው “ወንህነሰ ንጽህቅ ለርእዮተ ገጽክሙ ፍስህተ ወለሰሚአ ዜናክሙ ወዜና ኩሎሙ መርዔትክሙ ቡሩካን ወዜና ኖሎትኒ እለ እምታህቴክሙ ይእቀቦሙ እግዚአብሄር በጸሎ ትክሙ ወመነኮሳትሂ እለ ውስተ ገዳማት ወአበው ቅዱሳን ወያብጽህ ለነ እግዚ“ በሚለው መመሪያ ጸንታችሁ መቆማችሁን ስናረጋግጥ ብቻ ነው።

“አረጋዊ መንፈሳዊ” የተባለው መጽሀፍም በመጀመሪያ ድርሳኑ ላይ “መፍትውኬ ለሰብእ ይትአቀብ እምተአርኮ ደቂቅ። ከመ ኢይርኮስ ልቡ በህሊና ዝሙት”ይላል። እንደገና “ፍናዌ መልእክት አርብዓ” በሚለው ክፍል ላይ **“ዕቀብ አዕይንቲከ እምርእየ ኩሉ ሕስው”** ካለ በኋላ “እስመ ያነቅህ ለፍትወትከ” ይልና፤ “ኢታፍቅር ሕጻነ” ይላል። ሁለቱን ሐረጎች “ኢታፍቅር ሕጻነ” የምትለውንና “እምተአርኮ ደቂቅ” የተባለችውን ሐረግ ብንተረጉማቸው በህዝብ መካከል ያላችሁን ህልውና ባዶ ያደርገዋል። በደፈናው ግን ሰው ከመነኮሰ በኋላ የተፈጥሮ ፍላጎቱን

ሊገታ የሚችለው ከሴትና ከህጻናት አካባቢ በመራቁ ብቻ መሆኑን ያመለክታል። በሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የደረሰው ክስረት ለማስረጃ በቂ ነው። ኦርቶዶክሳዊቷ መመሪያችን የምትደነቀው ሰባዊ ባህርይን ሳትደብቅ፤ ጽድቅን ሳትለቅ በዘረጋችው መመሪዋ ነው።

በኢሀደግ ዘመን ካለችው ከኛ ቤተ ክርስቲያናችን በቀር፤ በሌሎች ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት በከተማ በህዝብ መካከል የሚኖር መነኩሴ የለም። በጥጋችሁ ያሉትን ሌሎች ኦርቶዶክሳውያንን ጠይቁ። መነኮሳት ከበአታቸው ሊወጡ የሚገባቸው ምንኩስናን የጀመረው አባ እንጦስ ያደረገውን ብቻ ለማድረግ ነው።

አባ እንጦስ ከሚሰቃየው ህዝብ መካከል ሆኖ ሥቃዩን ለመካፈልና ለማጽናናት ከገዳሙ ወጥቶ ወደ እስክንድርያ ከተማ ገባ። በህገ አራዊት ወደ ሞት የሚወሰዱትን ሰዎች ከፊታቸው ቀድሞ ከህገ አራዊት ወታደሮች ጋራ ተጋፈጠ። ከእስረኞች ጋራ ታሰረ። እስረኞችን በጸሎቱ እና በድፍረቱ አጠነከራቸው። በሱ ምክንያት እሱን በተከተሉት ካህናት መነኮሳት ላይ በህገ አራዊት የሚመራው መንግስት የሚያስፈፈራ የሞት ቅጣት አወጀባቸው። አንጦንስ ይህን ሲሰማ ቀጥ ብሎ በህገ አራዊት ወደ ፈረደው ዳኛ ሄደ። "He declared in a thunderous voice before him that he would never forsake his children ,but would stand by them to the very end. To the believers who watched him speak "his appearance was like unto that of the Angel of Light. (Page 61) ተብሎ ከተጻፈው ታሪክ እንደምንረዳው፤ በህገ አራዊት የሚመራው ማክስምያኖስ የተባለው ሰው ሊቋቆመው አልቻለም። በእንጦስ ተሸነፈ። እንጦንስ ሁሉን ካስተካከለ በኋላ ወደ ገዳሙ ተመለሰ። ህዝቡም በልቅሶ ወደገዳሙ ሸኙት ይላል።

ምንኩስና በህገ አራዊት የሚታወጅ መከራ በህዝቡ ላይ ሲደርስ ህዝቡን በሰላማዊ ሰልፍ ለመምራት ካልሆነ በቀር በከተማ መኖር ቀርቶ መታየት የለባችሁም። ይህን ስል ምስክሬ መጻህፍት ብቻ አይደሉም። በመላ ኦርቶዶክሳዊያን የተመሰረቱት ገዳማትና በውስጥ የሚኖሩት መነኮሳትም እየመሰከሩ ናቸው።

ከገዳም መወጣት ያለባችሁ የህዝቡን ችግር በግንባር ቀደም ለመጋፈጥ ከሆነ፤ እስቲ አሁን ያላችሁበትን እዩት! ጥሮ ግሮ መኖርን ሸሽታችሁ፤ በድሎት ለመኖር አቅዳችሁ ለራሳችሁ ምቾት በሰራችሁት ዳስ ለመኖር እንጅ፤ ጻድቃን ህዝብ እንዲጸድቅ እንረዳለን ብላችሁ እንዳልሆነ የከበባችሁ ሰው እየተናገረ ነው። በአባ ኢጋግዮስ ላይ የደረሰበት እንዳይደርስባችሁ አስቡ!

- ካህናት

ጴጥሮስ የክርስቶስን ዓላማ ረስቶ ከምድራዊ ነገር ጋራ አገናዝቦ ለመኖር በወሰነው ፍላጎቱ፤ ክርስቶስን "አይድረስብህ" ባለ ጊዜ "ዘወር በል ከፊቴ አንተ ሰይጣን" ቢባልም፤ ተግሳጹ ለመስማት ዘገየ። እኛም ከየ አቅጣጫው የሚሰነዘርብንን ተግሳጽ ከመስማት ይልቅ የየራሳችንን ዳስ እየሰራን በመኖር ላይ ነን። ለጠቅላላዋ ቤተ ክርስቲያንና ለህዝብ አልቆንም። በጥምቀት የታወጀው ጽድቅ ይቅርና "አቻ ላቻ) ሚዛናዊ ፍርድ ተገፎ በህገ አራዊት እጅ በወደቀበት ጊዜ ብዙዎቻችን በካባችን ተጠቅለለን ተኛን። በቤተ መቅደስ ተገቢ ያልሆነ ነገር ተፈጸመ ብሎ የዲሲ ህዝበ ክርስቲያን በተንቀሳቀሰበት ወቅት፤ነገሩ ይጣራ እውነት ከሆነ የተከሰሰው ካህን ዘወር ይበል፤ ከማላት ይልቅ ስህተቱን በተቃወሙት ሰወች ላይ መሳለቅ ጀመርን። ታዲያ እኛ ነን የጥምቀቱን በዓል መምራት የምንችለው?

ይህን እንድል ያስገደደኝ ዲሲ ላይ በተፈጠረው ስህተት፤ ችግሩን ለመፍታት ከየአጥቢያው ክርስቲያኖች መጥተው እኔም ተጋብዥ በተገኘሁበት የታዘብኩት ነገር ነው። በስብሰባው ላይ የተገኙት ምእመናን ከሰሙ ባካባቢው ያሉት ካህነት እነሱ ሳይሰሙ ቀርተው ነው? እንዲያውም አለመሰልጠና በማያገባንም እንደገባን አድርገው የተገኘነውን የወቀሱንና የሳቁብንም ገጥመውኛል። እነዚህ ሰዎች የነሱ ሙብት ሲነካ ቤተ ክርስቲያን የምትለውን በመጣስ ወደ ፍርድ ቤት የሄዱ ናቸው። ታዲያ በኛ ላይ የተሳለቁና የቀለዱ ካህናት "ኢትኅበሩ ምስለ እለ አልቦሙ ፍሬ ምግባሮሙ ዘጽልመት ኩለንታሆሙ። አላ ገስጽዎሙ። እስመ በዘ ጽሚት ይገብሩ ኀፍረተ ለነገር" ኤፌ ፭፡፲፩ የሚለውን እንኳን ያነበቡ ሲነበብ የሰሙ ናቸው ማለት ያስችላልን? ይህ ጠባይ ያለን ካህናት መገሰጸ የለብንምን? እሁድ እሁድ ከሰማይ የወረድን ቅዱሳን መላእክት መስለን ንስሀ ግቡ! እያልን የምንናገረው ለዳቧችን እንጅ ህዝቡን ለንስሀ ለማዘጋጀት እንዳልሆነ ግልጽ አይደለምን? ይልቅስ ይህ ህዝብ ከሰመመኑ ነቅቶ ዲዮቅልጥያኖስ በአባ ኢጋግዮስ ላይ እንዳደረገው የምንወደውን ወርቅ አቅልጦ እስኪግተን ድረስ አንጠብቅ።

በህግ ጋብቻ ያለን ካህናት "ሚስቱን ልጆቹን እርሻን ያልተዎ ለኔ ሊሆን አይችልም" የተባልነው እኛ እንጅ መነኮሳት አይደሉም። ስለዚህ በህገ አራዊት የሚካሄደውን ደባ መቃወም እኛን አይመለከትም። የቤተ ሰብ ሀላፊነት አለብን በማለት ታላቋ ቤተ ክርስቲያናችን ስትናወጽ ወገን ሲንገላት በቤተ መቅደስ መደበቅ ቤተ መቅደሱን ማርከስ ነው። ቅዳሴውን ወደ መተዳደሪያነት ቀየርነው። ይህን ቤተ ክርስቲያናችን የምትቀበለው አይደለም።

መጻሕፍትን እንመልከት! "አሮን ነደቀ ምሥዋዐ አንጻሮ ወአዖደ እንዘ ይብል በዓለ እግዚእ ጌሰም"(ዘጸ ፴፪፡፭) ከህገ አራዊት (እንስሳ) ባለመላቀቃቸው በእንስሳ ምስል እግዚአብሔር ያልፈቀደውን ለህዝብ የማይጠቅም ባዶ በአል ለማድረግ ከተነሱት ጋራ አሮን ተባብሮ የራሱን ምስል ተከለ "ይበልኡ ወይሰትዩ ወተንሥኡ ይዝፍኑ ወይትዋነዩ(፴፪፡፮) በጽላቱ ላይ ከተጻፈው ፍትህ ርትእ ጋራ ተስማሚ ባልሆነ፤ ነገር ግን

በሕገ አራዊት እየተገፉ ሥጋቸው የፈቀደውን እያደረጉ ጽላቱን ሊቀበሉ ሞከሩ። ጽላቱ ከሕገ አራዊት ጋራ አንድነት ስላልነበረው ከነሱ ጋራ አልዘለቀም። እንደዚሁ ሁሉ ለራሳችን መተዳደሪ እቅድ በመዘርጋት የህዝቡን ያገር ናፍቆትና ትዝታ በቤተ መቅደስና በአውደ ምህረቱላይ እንደ ክራር እየመታን የምንፈጽመው ለጣኦት ከሚደረግ ስህተት የራቅ አለመሆኑን ልንረዳ ይገባናል። ህዝብ ሲጎዳ ህዝቡ "ሰማይ ስሚ መሬትም አድምጭ" እያለ ሲጮህ ከህዝቡ በዘረፍነው ገንዘብ እየተንደላቀቅን ራሳችንን ከህዝብ ለይተን በቤተ መቅደስና በአውደ ምህረቱ ላይ በምናደርገው አገልግሎታ ብቻ ከህዝብ ለመገናኘት መሞከር በህዝብ ላይ መሳለቅ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባናል።

- <u>ምእመናን</u>

በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የተጠመቃችሁ አሁንም እምነታቸውን ጠብቃችሁ ያላችሁ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ሆይ! የበዓሉን ምሥጢር ላካባቢያቸው እያካፈላችሁ ክርስቶስ በጥምቀቱ ካወጃት ጽድቅ ላይ ለመድረስ ከጥንት ጀምሮ በመታገል እንደኖሩት አባቶቻችሁ በነቂሃ ሕሊና; በአንቃእዶ ልቡና በያላችሁበት በየደረሳችሁበት የጥምቀትን በዓል አክብሩት።

በበዓላት ብልጭ የሚሉ ትዝታዎች  ባምስቱ ህዋሳቶቻችን በማየት፤ በመስማት፤ በመዳሰስ፤ በመቅመስና በማሽተት  አማካይነት ገብተው በዓዕምሮ ብቻ ሳይወሰኑ በህዋሳቶቻችን ሁሉ ላይ ተንዝጉዘዋል። ለበዓሉ በምናዘጋጃቸው ምግባችን ልብሳችን ቋንቋችን ላይ ይሰፍናሉ።  በዘፈን በደስታና በሀዘን አዲስና ትኩስ ሆነው እንደገና ይቀሰቀሳሉ። ጠቅላላው ስሜታችን በተጎዘጎዘው ትዝታ ብቻ ሳይሆን በተሸከመው ቁም ነገር ጥምቀትን ለማክበር በስሜት እንቀሳቀስ!

በትዳር ሀለፊነት ተጽእኖ በዓላቱ እንዴት ለምን እና በማን እንደተጀመረ ቁም ነገሩን አንርሳ። በትዳር ተወስኖ ልጅ በማሳደግ መኖር በዓል የተሸከመውን መልእክት ለመረዳት መጋረጃ ይሆናል። የተጀመረበትን ዓላማ እና ምሥጢር ያስለቅቃል። ይዘቱንና ጥቅሙን ለመረዳት እንድንጥር ከማድረግ ይልቅ በሰመመን ውስጥ ይከተናል። ግልብ ወደ ሆነ ስሜት  በመጎተት  በዓሉን ለማክበር በሚደረገው ሽር ጉድ ላይ ብቻ እንድናተኩር ያደርገናል። ከዚህ <u>ደረጃ ላይ ከደረሰን  በሰመመን የምናከብራቸው በዓላት ለራሳችን  ከሚሰጡን ጥቅም ይልቅ በራሳችን ላይ የሚያስከትሉብን ጉዳት እጅግ ይከብዳል።</u>

"በጻህክሙ ኀበ ጽዮን ሀገረ እግዚአብሄር ህያው እንተ በሰማያት  መንፈሰ ጻድቃን ፍጹማን"(ዕብ <u>፲፪፡፳፪__፳፬</u>) እንዳለው፡- ፍጹማን የሆኑ መንፈሰ ጻድቃን ከሚኖሩባት ከእግዚአብሔር ከተማ መድረስ የምንችለው ክርስቶስ በጥምቀቱ ባወጀልን ጽድቅ ነው። አገራችንን ኢትዮጵያንም ከገባችበት አረንቋ ማውጣት የምንችለው እያንዳንዳችን በተኩላ እንደተበተነ የበግ መንጋ ሆነን እንዳንቀር ለራሳችን እየተጠነቀቅን፤ ያልገባውን ወገን ክርስቶስ የወጃትን ጽድቅ ማሳየት ስንችል ነው። ይህች ጽድቅ ሕገ አራዊትንና ሕገ ኦሪትን ሰንጥቃ የወጣች በልባችን ተተክላ  ጫፏ በሰማይ ባለችው ከተማ ዘልቃ የገባች የእግዚአብሔር መከዳ ናት። ይህች ጽድቅ ከልባችን እንዳትነቀል እግዚአብሄር ይጠብቅልን እያልኩ፤ ለከርሞ ካደረሰን እንደ ደመራው በዓላችን በዓለም አቀፍነት ተመዝግባ የሰው ልጅ ሁሉ የሚሳተፉት እንድትሆን ለማድረግ ያባቶቻችንና የናቶቻችን አምላክ ይርዳን። በማለት እሰናበታችኋለሁ።

ለሌሎች ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ጦማሮች የሚከተለዉን ድህረ-ገጽ ይመልከቱ::
<u>http://www.medhanialemeotcks.org/</u>